# አድርባይነት እና ጥልቅ ተሃድሶ

ሰለሞን ሽፈራው 12-20-16

ኢህአዴግ መራሹን የኢትዮጵያ ሕዝቦች የትግል መስመር ከሚፈታተኑት ውስጣዊ ድክመቶች አንዱና ምናልባትም ዋነኛው የአድር ባይነት ችግር የተጠናወታቸው አባላት ቁጥር እየተበራከተ መምጣቱ እንደሆነ ራሱ ግንባሩም ጭምር ሲናገር ያደመጥንበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም፡፡ ለምሳሌም፤ በ2005 ዓ.ም ባህርዳር ከተማ በተካሄደው የኢህአዴግ 9ኛው መደበኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ አድርባይነት አመራሩን ሳይቀር የሚፈታተንበት ሁኔታ እንዳለና እንደአንድ የሥርዓቱ አደጋ ተወስዶ መፍትሔ ሊፈለግለት እንደሚገባ ያሳሰቡ ከፍተኛ የድርግቱ ኃላፊዎች እንደነበሩ ማስታወስ ይቻላል፡፡

በ9ኛው የኢህአዴግ መደበኛ ጉባኤ ላይ ጉዳዩን ያነሱት፤ የህ.ወ.ሐ.ት ሊቀመንበርና የትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳደር አቶ ዓባይ ወልዱ ሲሆኑ፤ እርሳቸው አድርባይትን መታገል እንደሚያስፈልግ ያሳሰቡበትን ንግግር ያሰሙት ደግሞ፤ የግንባሩ ሊቀመንበርና የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ መድረኩን ሲመሩ "በሉ እስቲ ስለቀጣዩ ስራችን የየራሳችሁን ሃሳብ ስጡ" የሚል ጥያቄ ማቅረባቸውን ተከትሎ ነበር፡፡ እናም ክቡር አቶ ዓባይ ወልዱ "ቀጣይ የትግል አቅጣጫችን በተለይም አመራሩን ከአድርባይነት ችግር እንዲላቀቅ ማድረግና ከዚያም ልማቱን ለማፋጠን የሚያስችለንን አገራዊ እንቅስቃሴ ይበልጥ ማቀጣጠል ነው የሚሆነው" ሲሉ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥያቄ ምላሽ ሰጡ፡፡

ከእርሳቸው ቀጥሎ የመናገር ዕድል ያገኙት አቶ አዲሱ ለገሰ "እንደኔ እምነት ግን በቀጣይ ልንሰራው የሚገባን አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ የሚሰማኝ መልካም አስተዳደርን የማስፈን ስራ ነው፡፡ ስለዚህም ሕዝብ እያስመረረ ያለውን የመልካም አስተዳደዘር ችግር የመቅረፍ ጥረት መቅደም ይኖርበታል እንጂ፤ ልማትና አድርባይነትን የመታገል ጉዳይ እንደ አንገብጋቢ አጀንዳ መነሳት ያለበት አይመስለኝም" ሲሉ የአቶ ዓባይን ሃሳብ ለመቃወም ያለመ የሚመስል አንድምታ ያለው አቋም የተንፀባረቀበት አስተያየት ሰንዝረው እንደነበር አይዘነጋም፡፡ ይህ የግንባሩ አንጋፋ የአመራር አካላት አቋም በይፋ የተንፀባረቀበት የባህር ዳሩ መደበኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ተጠናቅቆ ሁሉም ወደየስራው ከተመለሰ በሁዋላ ግን፤

አንድም እንኳን አድርባይት የሥርዓቱ አደጋ ስለመሆኑ ትንፍሽ የሚል የድርጅት አካልም ሆነ አባል አልተገኘም፡፡

እናም እኔ የአቶ ዓባይ ወልዱን ሃሳብ እጋራው ስለነበር የጉዳዩ አስፈላጊነት እንደዘበት ተድበስብሶ "የውሾን ነገር ያነሳ ዋሾ ይሁን" እንደሚለት የሚቆጠር ቸልታ እንዲውጠው መደረጉ ተገቢ እንዳልሆነ ለመጠቆም "አድርባይነት እንደመቻቻል ሲቆጠር" በሚል ርዕስ የጫጫርኩትን አንድ መጣጥፍ በ2006 ዓ.ም መጨረሻ ግድም አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ታትሞ እንዲወጣ ማድረጌ አልቀረም፡፡ ልክ በዚያው ሰሞን፣ ማለትም ነሃሴ 2006 ዓ.ም ላይ፣ ክቡር የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ የኢህአዴግ ወጣት ሊግ አባላት ጋር በተወያዩበት አንድ የምክክር መድረክ "ድርጅታችን ኢህአዴግ አድርባይነት የሥርዓቱ አደጋ ነው ብሎ ስለገመገመ በተለይም እናንተ ወጣቶች የአድርባይነትን ችግር አምርራችሁ መታገል ይኖርባችኋል" የሚል ማሳሰቢያ ሲሰጡ በመስማቴ ደስ ብሎኝ እንደነበርም ማስታወስ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

ከፋቱ ግን፣ ከዚያን ቀኑ የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማሳሰቢያ በኋላ አድርባይነት የሥርዓቱ አደጋ ስለመሆኑ የሚያወሳ ንግግር ከአንድም ሌላ የመንግስትም ሆነ የድርጅት አባል አንደበት የሰማሁበት አጋጣሚ አልነበረምና አሁንም ነገሩ እየከነከነኝ ድፍን አንድ ዓመት አለፈ፡፡

አሁን በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የማድረግ ጥረት እንደተጀመረ እየተነገረለት ያለውን የጥልቅ ተሃድሶ ንቅናቄ ለስሙ በሚመጥን ስፋትና ጥልቀት ለማሳካት ይቻል ዘንድ፣ እርስ በርስ የመተጋገል ፀር ስለመሆኑ የሚታመንበት የአድር ባይነት ችግር የሚገለፅበትን አመለካከት በቅጡ ማውገዝን ማስቀደም አይጠበቅብንም ወይ? ወደሚለው ቁልፍ ጥያቄ ከማለፌ በፊት ግን፣ አንድ የሃተታዬን ማጠንጠኛ መሰረተ ሃሳብ ያዳብርልኛል የምለውን ተያያዥ ገጠመኝ አንስቼ ለማስታወስ ልሞክር፡፡ ስለሆነም፣ ቅዳሜ 25ኛውን የግንቦት 20 ድል የብር እዮቤልዩ በዓል ምክንያት በማድረግ ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል አዘጋጅቶት ወደነበረው የግማሽ ቀን የፓናል ውይይት መድረክ ልመለስና እዚያ ላይ ታድሜ ስለታዘብኩት ተያያዥ ጉዳይ የሚያወሱ ጥቂት ጠቃሚ ነጥቦችን እንደሚከተለው አሳጥሬ ላቅርብ፡፡

25ኛውን ዓመት የግንቦት 20 የድል በዓል ምክንያት በማድረግ ግንቦት 29 ቀን 2008 ዓ.ም ዋልታ አዘጋጅቶት የነበረውን የፓናል ውይይት የመሩት፣ በህንድ የኢፌዲሪ መንግስት ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ዶክተር ገነት ዘውዴ የዕለቱ የማዕከሉ ሰራተኞች በዓል የክብር ዕንግዳ ተደርገው እንደተገኙ ልብ ይባልልኝና ከእርሳቸው የአወያይነት ሚና ጋር በተያያዘ መልኩ ስለሆነው ጉዳይ እናንሳ፡፡ ማለትም፣ ክብርት አምባሳደሯ ለፓናል ውይይቱ መዘጋጀት ምክንያት የሆነው የግንቦት 20 ድል በዓል ሲከበር መወሳታቸው ስለማይቀረው ትሩፋቶቹና ለመላው የአገራችን ሕዝቦች ስላስገኘላቸው ጠቀሜታ ገለፃ ካቀረቡ በሁዋላ፣ ኢ.ህአዴግን ሲፈታተኑት ስለሚስተዋሉት የራሱ ውስጣዊ ድክመቶች በወቅቱ አለመፈታት አስታውሰው "እስቲ ኢ.ህአዴግ ችግሮቹን ለምን በደንብ መፍታት እንዳቃተው እናንተ ንገሩኝ?" ሲሉ ለፓናል ውይይቱ ተሳታፊዎች የሰነዘሩት ጥያቄ ነበር፡፡

እናም ለጥያቄያቸው ምላሽ ለመስጠት የሞከሩት የፓናል ውይይቱ ተሳታፊዎች በሙሉ "ኢ.ህአዴግ ውስጣዊ ችግሮቹን በቅጡ መርምሮ ትርጉም ያለው መፍትሔ ሲሰጥ ላለመስተዋሉ ዋነኛው ምክንያትማ አድርባይነት ስር እየሰደደ መምጣቱ ነው!" የሚል ተመሳሳይ አቋም ማንፀባረቃቸው ነበር ጉዳዩን በዚህ መጣጥፌ ላይ እንዳወሳው የገፋፋኝ፡፡ ይልቁንም፣ ክብርት አምባሳደር ገነት ዘውዴ አጻራሹን ለሞላው የፓናል ውይይቱ ተሳታፊ ያቀረቡትን ሁላችንንም በእኩል መጠን የሚመለከተንን ወቅታዊ ጥያቄ ለመመለስ እጃቸውን ያወጡት ሶስት ወይም አራት ያህል የህወሐት ነባር ታጋዮች ብቻ እንደነበሩ ማስታወስና የጉዳዩን አሳሳቢነት ለምን ሌላው ታዳሚስ እንደነርሱ ሳይገነዘበው ቀረ? የሚለውን ቁልፍ ነጥብ ለማየት የሚጋብዝ መሰረተሃሳብ ማንሳት ተገቢ መስሎ ይሰማኛልና ነው እኔም ወደዚያ የግማሽ ቀን መድረክ በትውስታ መልክ የመለስኳችሁ፡፡

ከምላሽ ሰጭዎቹ የህ.ወ.ሐ.ት ነባር ታጋዮች አንዱ "ድሮ በትጥቅ ትግሉ ዘመን አድርባይነት እጅጉን የሚያስነውርና የሚያሳፍር ነገር ተደርጎ ይወሰድ ስለነበር አንትና እኮ አድር ባይ ነው ከተባለ በቃ ያን ሰው የሚቀርበው ወይም ደግሞ የሚያምነው አይገኝም ነበር፡፡ አሁን እየሆነ ያለው ግን በተቃራኒው አድርባዮች ናቸው የሚከበሩት፣ ታዲያ እንዴት እውነቱን ተነጋግሮ ችግሮች እንዲፈቱ ማድረግ ይቻላል? ስለዚህ እኔ ኢ.ህአዴግ ድክመቶቹን በወቅቱ እንዳይቀርፍና አሁን ለሚስተዋለው ውስጣዊ ችግር እንዲጋለጥ እያደረገ ያለው ዋነኛ ምክንያት በተለይም የአድርባይነት አመለካከትን የማውገዝ የትግሉ

ፖለቲካዊ ባህል ስለቀረ ይመስለኛል" ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተው ነበር። ሌሎች በወቅቱ አስተያየት የሰጡት ተሳታፊዎች ያነሱት ተመሳሳይ ሀሳብ ነበር።

ከዚህ በመነሳትም፤ ችግሩ እያንዳንዱን የዛሬዋ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጉዳይ እንጂ፤ በወቅቱ ዝግጅቱ ላይ ለታደሙት የዋልታ ሰራተኞች ብቻ የሚተው ጉዳይ እንዳልሆነ ከወዲሁ የጋራ ግንዛቤ ሊወሰድበትና መፍትሔ ሊበጅለት ይገባል እላለሁ፡፡ አለበለዚያ ግን አሁን ላይ የተጀመረውን የጥልቅ ተሃድሶ መርሐ-ግብር በሚጠበቀው መልኩ አሳክተን ሥርዓቱን ከተጋረጠበት አደጋ መታደግ ይቻላል ብሎ መገመት የሚከብድ ይመስለኛል፡፡ ይህን የምልበት ምክንያትም ደግሞ የጥልቅ ተሃድሶውን መርሐ-ግብር ለመንደፍም ሆነ ንቅናቄውን ለመጀመር እንድንገደድ ያደረገን የሀገራችን ወቅታዊና ነባራዊ ጥሬ ሀቅ በቅጡ ሲጤን የሚገለፅልን እውነታ፣ የስርዓቱ አሳሳቢ አደጋዎች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ከሚዲያ ነክ የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት ፖለቲካዊ አመለካከት ጦርነት ጋር ተያያዥነት ካለው ችግር የሚመነጩ መሆናቸውን ያረጋግጥልናልና ነው፡፡

ስለዚህ የመገናኛ ብዙሃን አውታሮቻችንን የሚያንቀሳቅሳቸው የሰው ሃይል ከመሰል ትምክህትና የጠባብ ብሄርተኝነት ፅንፈኛ አስተሳሰብ በፀዳ ሙያዊ ስነምግባር የተገራ አስተማማኝ ቁመና እንዲኖረው በማድረግ ረገድ መስራት የሚገባንን የቤት ስራ በቅጡ መስራት ሳንችል፤ የጥልቅ ተሃድሶ መርሐ ግብሩ ንቅናቄ የሚፈለገውን ያህል ትርጉም ያለው አወንታዊ ተፅእኖ በሚያሳድር ስፋትና ጥልቀት ተፈፃሚ ይሆናል ብሎ መገመት ያዳግታል፡፡ ስለሆነም ይህ ጉዳይ ከወዲሁ እንዲታሰብበትና መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ለመጠቆም እሻለሁ፡፡ ሌላው የመጣጥፌ ማጠንጠኛ ከሆነው የነገረ-አድርባይነት መሰረተ ሃሳብ ጋር ሳላነሳው ማለፍ የማይኖርብኝ አንድ ተጨማሪ ጉዳይ፤ የቀድሞው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የአገር መከላከያ ሰራዊት ኢታማዦር ሹም ሌትናል ጀነራል ፃድቃን ገብረ ትንሳኤ፤ ባሳለፍነው 2008 ዓ.ም መጨረሻ ላይ "የአገራችን ወቅታዊ ችግሮችና የመፍትሔ ሃሳብ" በሚል ርዕስ ሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ባቀረቡት ተከታታይ ፅሁፍ "አድርባይነት የስርዓቱ ችግር ሆኗል" ሲሉ አጠንክረው የገለጹበት አግባብ እንደነበር ነው፡፡

"… በተለይም ደግሞ የ1993ቱን የሃወሐት አመራር መከፋፈል ተከትሎ በሁሉም የኢህአዲግ አባል ድርጅቶች መካከል የነገሰው እርስ በእርስ የመፈራራትና የመሰጋጋት ስሜት የውስጠ ዴሞክራሲ ምህዳሩን ስላጠበበው ነው አድርባይነት እየተስፋፋ የመጣው

የሚል እምነት አለኝ እኔ በግሌ” ያሉት የቀድሞው ጄነራል፤ ክስተቱ ኢህአዴግነትን ለተራ የግል ጥቅም ማሳደጀነት ብቻ የሚፈልጉት ብልጣ-ብልጥ አባላት እንዲበራከቱና በአንጻሩም ለትግሉ መሠረታዊ ዓላማዎች በፅናት የሚቆሙ እውነተኛ ታጋዮች ቁጥራቸው እያነሰ እንዲመጣ ያደረገ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩን አስምረውበታል፡፡ ለነገሩ ኢህአዲግ ራሱስ ቢሆን” “ስልጣንን ለሕዝብ ጥቅም የሚሰጡ መንግስታዊ ተግባራት ማከናወኛ ከማድረግ ይልቅ ለግል ፍላጎት ማሳኪያ አድርጎ የመገልገል መሠረታዊ ችግር አመራሩንም ጭምር እንደሚፈታተነው በግምገማ አረጋግጫለሁ” የሚል ይፋዊ መግለጫውን በስራ አስፈፃሚው አማካኝነት አውጥቶ የለ? ስለዚህ አድርባይነት ከሚገለፅባቸው መንገዶች አንዱና ምናልባትም ዋነኛው ይሄው ችግር ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ይመስለኛል፡፡ ከዚህ አኳያም ነው አድርባይነትና ጥልቅ ተሃድሶ በሚል ርዕስ ስር ጉዳዩ ተገቢ ትኩራት እንዲሰጠው ለማስገንዘብ የሞከርኩት፡፡ መዓ ሰላማት!